Institute of Development & Education for Africa, Inc.
1199 Whitney Ave Suite 523 Hamden, Ct 06517 Tel: 203-789-1990 or 203-747-2763

ሐምሌ 9 2006 July 16, 2014

# የኢትዮጵያ የፖለቲካ ህዋና አቅጣጫ
## የመንግሥት፣ የተቃዋሚ ቡድኖችና፣ የሕዝቡ ታሪካዊ ግዴታ

ገላውዴዎስ አርአያ ዶ/ር

የዚህን ጽሑፍ ትኩረት በቅድምያ ከአርእስቱ ለመተንበይ እንደሚቻል ሁሉ በዋናነት ለአንባብያን መልእክት ማስተላለፍ የምፈልገው ኢትዮጵያን አስመልክቶ ሁላችን ሐላፊነት መሸከም እነዳለብን ሆኖ፣ በተለይ ግን በመንግሥት፣ በተቃዋሚ ቡድኖች እና በሕዝቡ ታሪካዊ ግዴታዎች ላይ በመንተራስ ልዩ ልዩ ዓበይት ነጥቦችን ሒሳዊና ገንቢ በሆነ መንገድ በማቅረብም ጭምር ነው። የዚሁ ጽሑፍ ዓላማ ከላይ እንደተገለጸው ሆኖ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ደግሞ በያሉበት ተመሳሳይ አስተዋጽኦ እንድያደርጉ መልእክት ለማስተላለፍም ነው።

ማንኛውም ጥናታዊ ጽሑፍ፣ የአስተያየት መጣጥፍ፣ ወይም አቃቂር ሚዛናዊና አንጻራዊ በሆነ መንገድ ካልተጻፈና፣ ጸሐፊው አመለካከቱና የትንታኔ ዘዴዎቹን ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ማገናዘብ ካልቻለ፡ ጽሑፉ በርካታ ግድፈቶችና ስሕተቶችን ሊያንጸባርቅ ይችላል። ስለሆነም ጸሐፊው ያሰበውን ግብ ከመምታት ይልቅ ውድቀትን ሊጎናጸፍ ይችላል። ይህ ያልኩበት ምክንያት ደግሞ በርካታ ተቃዋሚ ነን የሚሉ እና የመንግሥት ደጋፊ የሆኑት ከሃገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን (Diaspora) እጅግ በጣም ጠባብ የሆኑ የፖለቲካ ትንታኔዎች በተደጋጋሚ ሲያቀርቡ በማየቴ ነው። ተቃዋሚዎቹ ባሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ጽልመተ ዓለም እንደሆነች አድርገው ሲያቀርቧት፣ የመንግሥት ደጋፊዎች ደግሞ አገሪቷ ወደ ምድረ ገነት እየተለወጠች መሆነኗን ለማሳየት ይሞክራሉ። እነኚ ሁለት ጽንፈኛ ፕሮፖጋንዳዎች ግን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ እጅግ በጣም የራቁ ስለሆኑ ፋይዳ የላቸውም። ለሃገራችንና ለሕዝባችን የሚጠቅሙ ነገሮችን ደግሞ ማበርከት አይችሉም።

ሚዛናዊና አንጻራዊ የሆነ ፖለቲካ ግን ምን ጊዜም ለሃገር ግንባታና ለሕዝቡ ጠቀሜታ ታላቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ይኸንን መንፈስ በመከተል ነው እንግዲህ በዚሁ ጽሑፍ ሂሳዊ ትንታኔዎችና ግንዛቤዎችን በማቅረብ የኢትዮጵያን አጠቃላይ የፖለቲካ ጉዞ ለማቅረብና ለመንግሥት፣ ለተቃዋሚ ቡድኖችና ለሕዝቡ ኃላፊነትን ማሸከም የፈለግኩት። ለዚሁ ግዴታ ግን በቅድምያ እኔም ተጠያቂ ነኝ። ባገር ጉዳይ ላይ ሁሉም ዜጋ ኃላፊነትን መሸከም አለበት። አለዛ “ኢትዮጵያ አገራችን” የሚል መፈክር ማንገብና ባንዴራን ማውለብለብ ብቻ ትርፉ የደንቃራ ፖለቲካ ነው የሚሆነው። ኢትዮጵያውያን ከጠባብ አመለካከትና ዝንባሌዎች ራሳቸውን ነጻ በማውጣት ያገራቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ምን እንደሚመስል መመርመር አለባቸው።

## የኢትዮጵያ የፖለቲካ ህዋ ምን ይመስላል?

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ መመርመርና መፈተሽ ከፈለግን መጀመርያ እንደ ማንኛውም የፖለቲካል ሳይንስ ተመራማሪ በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት ባህርይ በጥሞና ማጥናት ይኖርብናል። ወደድንም ጠላንም አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የኢሕአዲግ መንግሥት ነው። አንዳንድ የተቃዋሚ ቡድኖች “የወያኔ መንግሥት” ይሉታል፣ ይህ ግን የተሳሳተ አባባል ነው። ለምን? 1) የአሁኑ ገዢ ፓርቲ የይፋ መጠርያ ወይም ስም ኢሕአዲግ ነው፣ 2) ኢሕአዲግ የአራት ፓርቲ ስብስብ ማለትም የወያኔ፡ የብአዴን (ድሮ ኢሕዴን)፡ ኦሕዴድ እና የደቡብ ኢትዮጵያ፡ የጋሪዮሽ ፓርቲ ነው። ከነዚሁ የበላይነት ያለው ወያኔ ለመሆኑ አንድም ሁለትም የለውም፣ ነገር ግን ሌሎቹ ሦስት ፓርቲዎች እንደ ተቃዋሚዎች አገላለጽ “ተለጣፊ” ወይም “ሆዳም” ተብለው የሚታለፉ ሳይሆን ከመደብ ትንተና አንጻር ካየነው አራቱ የኢሕአዲግ ስብስቦች በአመለካከት (ርእዮተ ዓለም) በመርሆና በጥቅም የተሳሰሩ ናቸው።

የኢሕአዲግ መኪና ዋናው ሞተር ወያኔ ሲሆን፣ የመሰራጫና የቁጥጥር ሞተርና ሌሎቹ የመኪናው ክፍላተ አካላት (ጎማዎቹ ሳይቀር) ደግሞ ብአዴን፡ ኦሕዴድ እና ደቡብ ኢትዮጵያ ናቸው። ኢሕአዲግ ከሌሎች የአገር ውስጥና የውጭ ተቃዋሚ ኃይሎች ስናስተያየው ደግሞ የራሱ ድክመቶችና ውጥረቶች (በቅርቡ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ በኢሕአዲግ ውስጥ ችግር አለ ብለዋል) እንዳሉ ሆነው ፓርቲው ግን ጠንካራና የተደላደለ ነው ማለት ይቻላል። በነገራችን ላይ ኢሕአዲግ የተጠናከረውና የተደላደለው በሚከተሉት ሦስት ምክንያቶች ነው፦

1) ኢሕአዲግ የገዢ ፓርቲ ስለሆነ ቁልፍ የመንግሥት አውታሮችን እንደ ደኅንነት (ፖሊስና የመከላከያ ሠራዊት)፡ ልዩ ልዩ ሚኒስትሮች፡ ፍርድ ቤቶች፡ የውጭ ጉዳይ፡ ፋይናንስ ወዘተ ስለሚቆጣጠር
2) ኢሕአዲግ ከ1997 ዓ.ም. (2005) ምርጫ በመማር በ2002 ዓ.ም. (2010) ምርጫ ላይ የጠፈ ዘመቻ በማካሄድ፣ ስራ በመፍጠር፣ መሬት በማደልና ሹመት በመስጠት ወዘተ የሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት መብቃቱ፣
3) የአገር ውስጥና የዳያስፖራ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች መሰነጣጠቅና መዳከም ለኢሕአዲግ አመቺ ሁኔታ በመፍጠሩና ተቃዋሚዎቹ በተጨማሪ የኢትዮጵያና የዓለም አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ማገናዘብ ስላልቻሉ በ2007 ዓ.ም. (2015) ምርጫም ኢሕአዲግ አቸናፊ ሆኖ እንዲሚወጣ አያጠራጥርም። እንድያውም ምርጫው ለይስሙላ ይደረግ እንደሆነ እንጂ እንደበፊቱ በመጠኑም ቢሆን ተቃዋሚዎቹ ድምጻቸውን የሚያሰሙበትና ኢሕአዲግን በግጥምያ ጥሪ የሚታገሉት አይመስለኝም። ገና ለገና ምርጫው ያለቀለት ጉዳይ (fait accompli) ነው የሚሆነው።

በሃገር ውስጥ የሚገኙ ተቃዋሚ ኃይሎች እንደ መድረክ፣ ሰማያዊ ፓርቲ፡ አንድነት፡ኢዴፓ፣ ወዘተ እስካልተጠናከሩ ድረስ የፖለቲካ ግባቸውን ይመታሉ ማለት ዘበት ነው። የሃገር ውስጥ ተቃዋሚ ኃይሎች የመጀመርያ ተግባራቸው ኢትዮጵያ-አቀፍ ፓርቲዎች መመስረት ነው፣ ዳሩ ግን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ህዋ ሳይፈቅድ በመቅረቱና የራሳቸውም ድክመት ተጨምሮበት ሕብረ-ብሄር ፓርቲ መመስረት አልቻሉም፣ ሊመሰርቱም አይችሉም፣ ምክንያቱም በሃገር-አቀፍ ሳይሆን በብሄር የተደራጁ ነውና። ከዳያስፖራ ተቃዋሚ ኃይሎች ግን የአገር ቤት ተቃዋሚ ቡድኖች ይሻላሉ፣ ዳያስፖራ በጎሳ ፖለቲካ የሰመጠና አቅጣጫውን የሳተ ነው የሚመስለው። የሚገርመው ግን ወያኔ ዘረኛ ነው እያሉ እነሱ በጎሳ መደራጀታቸው ነው።

ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጽሑፎቼ እንዳመለከትኩት ሁሉ ማንኛውም ተቃዋሚ ኃይል ‘የኢትዮጵያ’ የሚል ስያሜ (ለምሳሌ ኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ፓርቲ) ቢቀበልና ቢጠቀምም ቅሉ የእያንዳንዱ ድርጅት የአባላት ቅልቅል አንድ ወጥ ወይም አንድ ብሄር ነው። የኢሕአፓ ዓይነቱ ሕብረ-ብሄርና አገር-አቀፍ አደረጃጀት አሁን ብርቅዬ ሁኗል። ይህ ከፍተኛ ድክመት ብቻ ሳይሆን የፈለገውን ጥረት ቢደረግም እነኚ አንድ ወጥ ፓርቲዎች ግባቸውን መምታት አይችሉም። በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተንጠልጥሎ ነው የሆነው።

ሌላ በጣም አስፈላጊ የሆኑትና ከፖለቲካ ህዋ ጋር የተቆራኙ ሁለት ነገሮች፣ ነገር ግን በተቀዋሚ ቡድኖች ትኩረት ያልተደረጉባቸው 1) የኢትዮጵያ የአሁኑ ትውልድ ወጣቶች (በሃያና ሰላሳ አምስት እድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን) የአስተሳሰብ ለውጥ፣ 2) የኢትዮጵያ ማሕበራዊ ገጽታ ናቸው።

የወጣቶች የአስተሳሰብ ለውጥን አስመልክቶ ከብዙ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎችና ሞያተኞች ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት በነበረኝ ሰፊ ግኑኝነት ጥናቱን ለማድረግ በቅችያለሁ። የኢትዮጵያ ማሕበራዊ ገጽታ ጥናታዊ ጽሑፍ በሚመለከት ደግሞ በ2005 ዓ.ም. (2013) ለተወሰኑ የዳያስፖራ ስብስቦች አቅርቤው ነበር፣ ግን በይፋ ታትሞ ለሕዝብ አልቀረበም። ለወደፊቱ ዕድሉን ካገኘሁ በሰፊው አቀርበዋለሁ።

አሁን ያሉት የኢትዮጵያ ወጣቶች እንደ ድሮው በፖለቲካ የተሰማሩና የሰመጡ ሳይሆን አብዛኞቹ በሞያዊ ሥራዎች እና በንግድ ላይ ያተኮሩ ወይም የተጠመዱ ነው የሚመስሉት። ለምሳሌ ከአዲስ አበባ፡ ባህር ዳር፡ አዳማ፡ አዋሳ፡ ሃረር፡ ጅማና መቐለ የጻፉልኝ ወጣት ሴትና ወንድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ስለ ትምህርትና ስለ ንብረተ-ተቋም (entrepreneurship) እንጂ ስለ ፖለቲካ በጥያቄም ይሁን በአስተያየት መልክ ያቀረቡት ነገር የለም። አንድ የወጣቶች ስብስብ ከመቐለ አዲስ ጋዜጣ ልንጀምር ነውና የሚቻል ከሆነ “ንብረተ-ተቋም እና የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ምሩቃን” አስመልክቶ ጽሑፍ ላክልን ስላሉ በደስታ ጥያቄአቸውን በመቀበል አግባብ ያለው ጽሑፍ ልኬላቸዋለሁ። ሌላ አንድ ኢትዮጵያዊ ወጣት “የውኃ እጥረቶች ችግር በኢትዮጵያ ለመቅረፍ የቀረቡ ሐሳቦች” በሚል ርእስ ላቀረብኩት ጸሑፍ በማድነቅና እርሱም በኒውዚላንድ ለድህረ-ምረቃ ትምህርት ተመሳሳይ ጥናት እንደሚያደርግ ገልጾልኝ ነበር።

ባጠቃላይ የወጣቱ አመለካከትና ዝንባሌ ሲታይ ወይ በንግድ ተሰማርቶ ሃብትን ማከማቸት ነው ወይም ደግሞ የራሱን የግል ሥራ ፈጥሮ ኑሮን ማቸነፍና የኑሮን ደረጃ ማስተካከል ነው። እንዲህ ያለ አመለካከት ደግሞ የኢትዮጵያን የፖለቲካ አቅጣጫ አወንታዊ በሆነ መንገድ ያስይዟል የሚል እምነት አለኝ። ታሪክን በቅጡ ከመረመርን ፡ የጥንት ሥልጣኔዎችና በካፒታሊስት የዕድገት ስልት በመጓዝ የበለጸጉ ሃገሮች ልማታዊ ዕድገታቸው ስኬታማ ሊሆን የቻለው ንብረተ-ተቋምና ንግድ መሠረት ስላደረጉ ነው።

ወደ ማሕበራዊ ገጽታ ከማለፌ በፊት የፖለቲካ ህዋን አስመልክቶ ገንቢ ነቀፌታን በማከል ላገባድደው እፈልጋለሁ። እንደ ማንኛውም ዘመንና የአገዛዝ ስልት በኢሕአዲግ ዘመነ መንግሥት በኢትዮጵያ በጎና መጥፎ ነገሮች ተከስተዋል። ማንኛውም ምሁር ደግሞ እነኚ ሁለት ተቃራኒ ክስተቶችን ሚዛናዊና አንጻራዊ በሆነ መንገድ ነው ማቅረብ ያለበት። ነገር ግን በጎ ጉዳዮችን ስጠቅስ ኢሕአዲጎች እንዲደሰቱ፣ መጥፎዎችን ስጠቅስ ደግሞ እንዲከፋቸው መሆን የለበትም። በአንጻሩ

ኢ.ሕአዴግ ሲነቀፍ ተቃዋሚዎች እንዲደሰቱ፣ ኢ.ሕአዴጎች ሲመሰገኑ ግን ተቃዋሚዎቹ ቅር እንዲላቸው መሆን የለበትም።

በነገራችን ላይ 'ሚዛን መጠበቅ' የሚለውን ሃረግ አሁን ያፈለቅኩት ጽንሰ-ሐሳብ ወይም መርሆ አይደለም። ለምሳሌ የዛሬ ዘጥኝ ዓመት ስለ አፄዎቹ (ቴዎድሮስ፡ የሐንስ፡ ሚኒልክ እና ኃይለሥላሴ) ስጽፍ ሚዛናዊና አንጻራዊ በሆነ መንገድ ስለጻፍኩኝ ያደረጉትን አስተዋጽኦ እና በጊዝያቸው የተከሰቱትን መጥፎ ነገሮችን አቅርብያቸዋለሁ። በተመሳሳይ መልኩ፡ የዛሬ 19ኝ ዓመት በደረስኩት መጽሐፌና አሁን በቅርቡ ታትሞ በወጣው ሌላ መጽሓፌ ይኸንን መመርያ በመጠቀም ነው ትንትኔዎችን ያቀናበርኳቸው። ሌላም ከዚሁ ጋር የሚሄድ ምሳሌ ለአንባብያን ማቅረብ እፈልጋለሁ፦ የድሮ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ African Development: Dead Ends and New Beginnings በሚል ርእስ ጽሑፍ አቅርበው ነበረና ጽሑፉን በሚመለከት አቃቂር አቅርቤ ነበር፣ በመግብያውም ላይ "የአፄ ኃይለሥላሴ 'ህይወቴና የኢ.ትዮጵያ እርምጃ' የተሰኘውን መጽሐፋቸው ማንበብ ከቻልኩኝ የመለስ ዜናዊ የማላነብበት ምክንያት የለኝም" በማለት ሐተታ አቅርቤ ነበር። ብርሃኑ ነጋ (ዶ/ር) "የነጻነት ጎኅ ሲቀድ" መጽሐፉን (እሥር ቤት ሆኜ የጻፍኩትን የሚለውን) አስመልክቶ ደግሞ አቃቂር ጽፌ ስለነበር የሚከተለውን አርእስት ነበር የሰጠሁት፦ "ለመለስ ዜናዊ ያልተነፈገውን ለበርሃኑ ነጋ ይሰጠዋል"። በኔ ዓይን ሁሉም አንድ ናቸው፣ አንደኛውን ጭራቅ ሌላኛውን መልአክ አድርጌ ማቅረብ አልችልም። ካደረግኩም ኅሊናየ ይወቅሰኛል፣ የእምነቴም ርትኡነት ይዛባል። ስለሆነም ለሰው በላውና አረመኔው ደርግ ሳይቀር እንኳ በመጀምርያው መጽሐፌ ላይ አንዳንድ በጎ ነገሮች እንደ ጸረ-መሃይምነት ዘመቻ፣ አማርቲና መልክ-ወኬና የኤለትሪክ ኃይል ማመንጫዎች፣ ግልገል ግቤ፣ በለሳ የእርሻ ፕሮጀክት፣ አሚባራ የመስኖ ሥራ፣ ኮምበልቻና ባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ ወዘተ እንዳበረከተ አድርጌ ጽፌዋለሁ።

ደርግ የኢ.ትዮጵያን ወጣቶች በገፍና በግፍ ስለጨረሰና ሕዝቡንም በቀይ ሽብር አዋጅ ለእርድ ስለዳረገውና በጠቅላላ ኢ.ትዮጵያ የመቅሰፍት እርግማን እንዲያንዣብብ ማድረጉና አገሪቷን በጨለማ ስለከታት ካደረጋው በጎ ሥራዎች የፈጸማቸውን ወንጀሎች ሰለሚያመዝኑ የኢ.ትዮጵያ ሕዝብ ለደርግ ነብሰ-ገዳዮች ይቅርታ ለማድረግ የሚከብደው ይመስለኛል። ያም ሆነ ግን ያደረጋቸውን አስተዋጽኦ የግዴታ መጻፍ አለባቸው።

የኢ.ሕአዴግ መንግሥት አስመልክቶ ደግሞ ከፍ ብየ ከጠቀስኳቸው ሚዛናዊ አመለካከቶች አንጻር ነው ማየት ያለብን። በኢ.ሕአዴግ ዘመነ መንግሥት ብዙ መልካም ሥራዎችን፣ በተለይም ልማትን አስመልክቶ፣ ተከናውነዋል። ከነዚህም በጎ ክንውኖች በቅድመ-ግንባር የሚጠቀሱት የመሰረተ ልማት (infrastructure) ተቋሞች እንደ በርካታ መንገዶችና የሐዲድ መስመሮች፣ የትምህርት ቤቶች መስፋፋትና የ31 ዩኒቨርሲቲዎች መገንባት፣ የገጠር ልማት በእርሻና በኤለክትሪክ ዝርጋታ፣ የጤና ኤክስተንሽን መርሃ-ግብር በጠቅላላ ኢ.ትዮጵያ፣ የልዩ ልዩ ግድቦች (ግልገል ጊቤ 3ት፡ ተከዜ፡ ተሃድሶ ወዘተ)፣ የአዲስ አባባ እና ሌሎች ትላልቅ ከተሞች (ባሕርዳር፡ መቐለ፡ አዳማ፡ አዋሳ፡ ሐረር፡ ደብረብርሃን፡ ደብረማርቆስ፡ ጅማ ወዘተ) በዘመናዊ መንገድ መገንባት፣ የቤቶች ህንጻዎች ስራ መደንፋት፣ እንዲሁም ተረስተውና ተንቀው የነበሩትን ብሔረ-ሰቦችና ብሔራት (አኙዋክ፡ ቤኒሻንጉል ግሙዝ፡ አፋር፡ የደቡብ ኢ.ትዮጵያ ሕዝቦች፡ ሶማሌ ወዘተ) ወደ ማእከላዊ የፖለቲካ መድረክ ማምጣት ናቸው።

በሌላ በኩል ግን ዴሞክራስን አስመልክቶ ኢ.ሕአዴግ ታሪካዊ ግዳጁን አልፈጸመም ማለት ይቻላል። የኢ.ትየጵያ አብዮት በ1966 ዓ.ም. እንደፈነዳ ለአጭር ጊዜ

የዴሞክራቲክ መድረኮች ተከስተው ነበር፣ ታድያ ምን ዋጋ አለው ደርግ የሚባል ነጣቂ አሞራ መጣና ሁሉንም ነገር አኮላሸ። ደርግ ከወደቀ በኋላ ደግሞ ዴሞክራሲ ያብባል ወይም ይነግሳል ብለን ስንጠባበቅ የጠበቅነውን ያህል ሊተገበር አልቻለም። በአዲሱ መጽሐፌ ስለ ዴሞክራሲ በሰፊው አቅርቤዋለሁ። እዚህ ላይ መጥቀስ የምፈልገው ነገር ቢኖር የዴሞክራሲ ግንባታ በኢትዮጵያ ለመንግሥት ብቻ የሚተው ጉዳይ እንዳልሆነና፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባጠቃላይ፣ ምሁራን ደግሞ በተለይ የመቻቻል ባህል ማጎልመስ እንደሚኖርባቸው ነው። የኢሕአዲግ መንግሥት ደግሞ ነቀፌታን መቀበል ይኖርበታል። ተጻራሪ አመለካከቶችን መቀበል እና ማክበር ይኖርበታል። ኢሕአዲግ የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ አካል ስለሆነ ብቻ ሳይሆን በትረ-ሥልጣኑም ስለጨበጠ በዚሁ የዴሞክራሲ ግንባታ ላይ ከፍተኛ ሐላፊነትን መሸከም አለበት። ስለሆነም የመናገርና የመጻፍ፣ የሰላማዊ ሰልፍ መብቶች ወዘተ በሕገ መንግሥቱ ብቻ የሰፈሩ ሳይሆን በተጨባጭ መተግበር አለባቸው። ስለሆነም ነጻ ጋዜጠኛነት እንዲኖርና ጋዜጠኞች እንዳፈለጉ እንዲጽፉ መፈቀድ አለበት፣ ዜጎችና ተቃዋሚ ኃይሎች ደግሞ ሳይፈሩ ሳይቸሩ (በእናት አገራቸው ነውና ያሉት) የውይይት መድረኮች እንዲመሩ፣ ሰላማዊ ሰልፍ እንዲያደርጉና መንግሥትን እንዲነቅፉ (ዘለፋ ሳይሆን ገንቢ ነቀፌታ) እንደ መብታቸው መታየት አለበት።

ከዚህ ከመቻቻልና ዴሞክራስያዊ መብቶች ባሻገር ግን ኢሕአዲግ ከተቃዋሚ ኃይሎችና ከሌሎች ክፍላተ አካላት በመንግሥት የመወሰን ስልጣን ሂደት ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ አለበት። ባሁኑ ጊዜ ለምሳሌ ከ547 የኢትዮጵያ የፓርላማ ወንበሮች 499 የኢሕዲግ ሲሆኑና 46 በደጋፊ ፓርቲዎች የተያዙ ናቸው፣ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ግን 2 ወንበር ብቻ ነው የተሰጠው። ይህ በእውነቱ የሚያሳፍር ነው። በ2002 ዓ.ም. በተደረገው ምርጫ፣ በዚሁ ጽሑፍ መጀምርያ እንደጠቀስኩት፣ ኢሕአዲግ እንደሚያቸንፍ ግልጽ ቢሆንም (ይህ ለታሪክ ድንገት-ደራሽ ክስተቶች ቦታ ሳንሰጥ ማለት ነው) በተቻለ መጠን ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በፓርላማውና በማእከላዊ መንግሥት ዘርፎች ውስጥ የሚሳተፉበት መንገድ መቀየስ አለበት። ለምሳሌ ኢሕአዲግ 400 ወንበሮች ካቸነፈ የተቀሩትን 147 ወንበሮች ለመድረክ፣ ለሰማያዊ ፓርቲ፣ ለኢዴፓ፣ ለአንድነትና ለሌሎች ፓርቲዎች ቢሰጡ የገዢው ፓርቲ እነዚህን ፓርቲዎች በማሸጋሸጉ ይመሰገናል እንጂ የሚጎድለውና የሚያሰገው ነገር አይኖርም። የገዢ ፓርቲ ሆኖ መቀጠሉ አይቀርምና።

የዴሞክራሲ ሂደት በኢትዮጵያ የተኮላሸ ቢሆንም ቅሉ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን አንዳንድ የዴሞክራሲ ነጸብራቆች በኢሕአዲግ ዘመነ መንግሥት ተከስተዋል ማለት ይቻላል። ለምሳሌ በልዩ ልዩ ከተሞች የሕዝብ ስብሰባዎች በተካሄዱበት ቍጥር ተሳታፊው ዜጋ በላሥልጣናቱን በጥያቄ፣ ነቀፌታና ክስ-አዘል ሐተታዎች ወጥሮ ይይዛቸዋል። የነዚሁ ዓይነተኛ ምሳሌዎች በባሕርዳር፣ በሃረር፣ በአዲስ አበባ እና በሃዋሳ የመሳሰሉት ከተሞች ከንቲባዎቹን ወይም የነኚ ከተሞች ሌላ የመስተዳደር ባለሥልጣናትን ሳይፈራ ይጠይቃል። በዓድዋና በአዲግራት በተካሄዱት ስብሰባዎች ሕዝቡ ብሶቱን ለባለሥልጣናቱ በግልጽ አሳምቷል። በሐምሌ 7 2006 ዓ.ም. (July 15, 2014) በተካሄደው የሕዝብ ስብሰባ ተሳታፊዎቹ "የመንግሥት ቤቶች አጀንሲ ሰራተኞች ለደንበኞች ግልጽነት የሰፈነበት አገልግሎት መስጠት አለበት" በሚል ዙርያ የጦፈ ውይይት አካሂደዋል። እንዲህ ዓይነት የሕዝብ ሸንጎዎች ከቀጠሉ የሕዝብ ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን የሚረጋገጠው፣ ለመሰረታዊ የዴሞክራሲ ባህል (political culture) ደግሞ አስተማማኝ መልህቅ ተጥሏል ማለትም ይቻላል። ይህ ባህል ከቀጠለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪካዊ ድል ተቀዳጀ ማለት እንችላለን። የዴሞክራሲ ፖለቲካ ባህል እየጐለመሰና እየሰፋ በመጣ ቍጥር ደግሞ ሕዝቡ የራሱን መብት የሚያረጋግጥበት ሁኔታ ከመፈጠሩም በላይ ባለሥልጣናቱም የግዴታ ግልጽነትና

ሐላፊነትን ይሸከማሉ። ይህ ሲሆን ብቻ ነው ደግሞ ዴሞክራሲ ያለጥርጥር ተረጋግጧል ማለት የምንችለው።

ሰፊው ሕዝብ በሃገር ግንባታ አወንታዊ ሚና መጫወት የሚችለው ደግሞ መሠረታዊ መብቶቹን ሲጠበቁለት ብቻ ነው። መብቱ ሳይጠበቅለት በልዩ ልዩ የልማት ውጥኖች እንዲሳተፍ ከተደረገ ግን ወይ ተገዶ ነው ወይም ደግሞ በይሉኝታ እንጂ በፈቃደኝነት የሚያደርገው ጉዳይ አይሆንም።

እንግዲህ ከፍ ብየ ለውይይት መንደርደሪያ ያቀረብኳቸውን አንዳንድ ዓበይት ነጥቦች፣ ማለትም የኢሕአዴግ መንግሥት፣ ተቃዋሚ ቡድኖች እና ሕዝቡ (በተለይም ምሁራን) ከፖለቲካ ባሻገር የኢትዮጵያን ታሪክ፣ የዓለም አቀፍ ግንኙነቶችና፣ የኢትዮጵያ ማሕበራዊ ገጽታዎችም በጥሞና መመርመርና ማጥናት ይኖርባቸዋል። ቀደም ብየ እንደጠቀስኩት እኔ በበኩሌ ማሕበራዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ በስነ-ሕብረተሰባዊ ዘዴ ላይ በመንተራስ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርቤ ነበር። ጽሑፉ ከሞላ ጎደል የሚከተሉትን ርእሶች ያካትታል፦

I) የኢትዮጵያ ማሕበራዊ ደኅንነት ጥናታዊ ጽሑፎች፦ ሀ) ፍችና የቤተ ሰብ መፍረስ፣ ለ) የቤት ሁከት፣ ሐ) የሴቶች ምጣኔ-ሃብታዊ ፍች በከተማ፣ መ) የኮረዳዎች እርግዝና ማሕበራዊ ችግር፣ ሠ) እናታዊ ሞት በኢትዮጵያ፣ ረ) የወጣት ሥራ አጥነት ችግር በአዲስ አበባ፣ ሰ) ጫት ቃሚ ወጣት በኢትዮጵያ፣
II) የማሕበራዊ ደኅንነት ግልጋሎት በኢትዮጵያ፣ ምሳሌዎችና ፍጆታ ዋጋዎች፣
III) እርሻና ማሕበራዊ ጥበቃ በኢትዮጵያ፣
IV) እርጅና እና ድህነት በኢትዮጵያ፣
V) ማሕበራዊ ችግሮችና ሕብረተ-ሱታፌ ስትራተጂ፣
VI) የኢትዮጵያ ስደተኞች ማሕበረሰብ፣
VII) አዳዲስ የፈለቁ ማሕበራዊ ገጽታዎች

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ርእሰ-ነገሮች በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የማሕበራዊ ደኅንነት ክፍለ-ትምህርት የድሕረ-ምረቃ ተማሪዎች ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች (theses) አቅርቧቸው ነበር።

የአንድ ሕብረተሰብ ማሕበራዊ ጉዳዮች ከፖለቲካዊ፣ ምጣኔ-ሃብታዊና ስነልቦናዊ ዘርፎች ተነጥሎ የሚታይ አይደለም፣ እጅግ ውስብስብ ባለ መንገድ የተቆራኙ ናቸውና። ከማሕበራዊ ጉዳዮች ተነጥሎ የሚተነተን ፖለቲካ እጅግ በጣም የተንጠለጠለና የተዛባ ፖለቲካ ነው የሚሆነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ተጨባጭ የፖለቲካ ህዋ ማጥናትና መመርመር ከፈለግንና ያገራችን የፓለቲካ አቅጣጫ አወንታዊ በሆነ መንገድ መቀየስ ታሪካዊ ሐላፊነታችን ነው ብለን ካመን ሕበረተሰባዊ ጥናቶችን ማካሄድ ግዴታ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ይህ ሓለፊነት የምሁራን፣ የተቃዋሚ ቡድኖችና የመንግሥት ነው፣ እንዲህ ያለ አመለካከትና ግንዛቤ ሲኖረን ብቻ ነው ደግሞ ኢትዮጵያ ለመጪው ትውልድ ጤናማ ቅርስ ማውረስ የምትችለው።

የደራሲውና የአፍሪቃ ልማትና ትምህርት ተቋም (አልትተ) መብት በሕግ የተጠበቀ ነው (2006 ዓ.ም.) All Rights Reserved. Copyright © Institute of Development and Education for Africa (IDEA) 2014